*ወ/ሮ ገነት ግርማ በተባበሩት መንግስታት ሰብዓዊ መብት መድረክ ላይ ቀረቡ*

የተባበሩት መንግስታት ሰብ ዓዊ መብት ካዉንስል ከ ፈብሯሪ 28 እስከ ማርች 25 ድረስ በጄኔቫ ከተማ ተካሂዷል። በዘንድሮዉ በ አስራ ስድስተኛ ስብሰባዉ ላይ ትምህርት ለእድገት የአፍሪካ ድርጅት አማካኝነት በመግኘት ወ/ሮ ገነት በተለያዩ አርስቶች ላይ ንግግር በማድረግ በኢትዮጵያ ህዝብና በስደትም ባሉ ወገኖች ላይ የሚደርሰዉን በደል አጋልጠዋል።

1. አጀንዳ ቁጥር 4 :<u>ተተኩረዉ መታየት ያለባቸዉ ሰባአዊ መብት ጉዳዮች</u>

በአፍሪካ ዉስጥ አዲስ ጎህ በመቅደዱ የተስፋ ጭላንጪል በመታየቱም በስደት ላይ ያሉ አፍሪካዉያን ወደ ዉድ አገሮቻቸዉ ሲመለሱ መታያታቸዉ የሚያስደስት ሆኖ ሳለ፤ በበርካታ የ አፍሪካ አግሮች ዉስጥ የሰባዊ መብት መጓ ደል ገና እንዳለ መሆኑን። ከአፍሪካ ቀንድ የሚሳደዱ ዘጎች በየቦታዉ በመሰቃየትና ለሞት በመዳረግ ላይ እንደሆኑ፤ ሃያላን መንግስታትም ከዚህ ቀደም እንዳሳዩት የሰባአዊ መብት ማክበርና ሪሴትልመንት ማዳራጀት ሳይሆን እትድረሱብን ፖለቲካ ማንገባቸዉ ከሰባዊ መብት የራቀ መሆኑን፤የአዉሮፓ አገሮች ስደተኞችን መለሰዉ መላክ እንደሌለባቸዉ፤ በሊብያ ጦርነት ዉስጥ አጣብቂኝ ዉስጥ የገቡት ወገኖቻችን መድረሻ ሲያጡ የታዉ ግድየለሽነት ከፉኛ እንደሚያሳዝነን ተገልጽዋል። ከስደትና ጦርነት ሁኔታም ባሻገር ኢትዮጵያዊያን ሴቶች በመካከለኛዉ ምስራቅ በዘመናዊ ባርነት እንደሚማቅቁ እና በአንጻሩ በተባበሩት መንግስታት ስብሰባዎች ዙርያ ስለሴቶች ጉዳይ ብዙ ኣኤግዚቢሽኖች ቢታዩም አቅቂዎች ብርታታቸዉ ፈጽሞ እንዳልቀነሰ ተብራርቷል። የመሬት በገፍና በግፍ በመሸጡ ገበሬዉ ከቀየዉና ከኑሮዉ ካለምንም ድጎማ መፈናቀሉ እድገት ሊኖር ቀርቶ ግፍና በደል መበራከቱ፤ያካባቢ መንከባከብ ቀርቶ ጥንታዊ ጫካዎች መመንጠራቸው ለወደፊቱም አስከፊ ሁኔታን መፍጠሩ ተዘርዝሯል።

2. አጀንዳ ቁጥር 6: <u>ዩኑቨርሳል ፔርዮዲክ ሪቭዩ በ ለባነን ላይ</u>

የአገሮች ጉዳይ በየተራቸዉ በሚቀርብበት አርስት ዙሪያ የሌባነን እድል በመገኘቱ የአግራችን ዜጎችን ሁኔታ በተመለከተ በሰፊዉ ለማቅረብ ተችልዋል። የሚቆምላቸዉ አገርና መንግስት ያጡት እህቶቻችን በተለያዩ የመከከላኛዉ ምስራቅ አገሮች ዉስጥ ከሌሎች ዜጎች የበለጠ ጥቃት እንደሚዳርስባቸዉ፤ ከመደብደብና መሰደብ ባሻገር እንደሚገረፉ ምግብ እንደሚከለከሉ፤ ከፎቅ እንደሚወረወሩ፤ አሲድ እንደሚደፋባቸዉ፤ እንደልባቸዉ መንቀሳቀስ እንደማይችሉ፤ ፓስፖርታቸዉን እንደሚነጠቁ በአጠቃላዩ በዘመናዊ ባርነት ዉስጥ እንደሚኖሩ ተዘርዝሮ ቀርቧል። ከአገራቸዉ ሲወጡ ህይወታቸዉን ለማሻሻልና ወገኖቻቸዉን ለመርዳት ከተቻለም ገንዛብ አጠርቅመዉ ለመማር አቅድ የነበራቸዉ ላቅመ ሄዋን ያልበቁ ትናንሽ ሴት ልጆች ባላሰቡበትና ባልጋማቱት ሁኔታ በግደታ ወደ የሰዉ ልጆች ሺያጭ መስክ ተወርዉረዉ በድብቅ ፋብሪካዎችና የ ሽርሙጥና መስኮች በመሰቃየት ላይ እንደሚገኙ፤ ተደፋፍረዉ ምስክርነት የሰጡትን ሴቶች፤የሚረዷቸዉን ጋዜጠኞች ማመስገንና ማበረታታት እንደሚገባ ተገልጽዋል።

3. አጀንዳ ቁጥር 8፡ ሰባዓዊ <u>መበትን ለመጠበቅና ለማሳደግ በየአገሩ ስለሚቋቋሙ ድርጂቶች</u>

በኢትዮጵያ ሰባዓዊ መብትን በተመለከተ፤ የወገንን መርዳት በተያያዙት ድርጂቶች ላይ ጥቃት ከመከሰቱ ባሻገር ድራሻቸዉ እንዲጠፋና መደራጀት ሆነ ተንቀሳቅሰዉ ለመስራት እንዳይችሉ መደረጋቸዉ፤መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጂቶቸንና መረዳጃ ተቋማትን በተመለከተ የተደነገገዉ ህግ 10% በላይ የርዳታ ገንዘብ ከዉጭ አገር መቀበል እንዳይችሉ መደረጉ የብዙ ድርጂቶችን ስራ በማስተጓጎል ላይ መሆኑን፤ የወገን አእርዳታ ላይ ይረባረቡ የነበሩትን የሴቶች፤የህጻናት ብሎም የጽኩማን ድርጂቶች በማስተጓጎሉ ወገኖች መድረሻ እንዳጡ ተገልጽዋል። ሰባዓዊ መብት ድርጂቶች ደፍረዉ በግፍና በገፍ የሚታሰሩትን፤ደብዛቸው የጠፉ ወገኖችን፤ በ ቶርጬር የሚማቅቁትን፤ብሎም ከህግ ዉጭ የሚገደሉትን ወገኖች ጉጋይ ሊያነሱና ሊከራከሩ ቀርቶ ህልዉናቸዉ ራሱ ጥያቄ ዉስጥ የገባ በመሆኑ አምባገነኑ አስተዳደር በማናለብኝነት ዬኢትዮጵያን ህዝብ በማሰቃዬት ላይ እንዳሚገኝ ተገልጾ ሲቪከስ የተሰኘዉም ድርጂት የ ዚህን አፋኝ ህግ በዝርዝር እንዳዋጋዘ ቀርብዋል።

4. አጀንዳ ቁጥር 9፡ <u>ዘረኝነት፤በዘርልዩነት ማጥቃትና ተመሳሳይ በደሎች</u>

ስደተኞችና ማይግረንትስ በዘራኝነት ሰለባ በመጠቃት ላይ እንዳሉ፤ በተለይም ከ አፍሪካ የሚመጡትን በተመለከታ በ አስከፊ ሁኔታ መብታጨዉን አልማክበርና ለማስጠጋት አለመፈለግ ብቫ ሳይሆን በየወደቡ እእየሞቱ በየድንበሮች ተረፍርፈዉ በ ዓለም ሚዲያዎች ላይ በመታየት ላይ መሆናቸዉ፤ ይሄ አሰቀቂ ሁኔታ አልበቃ ብሎ ዛሬ ደግሞ በ ሊብያ ሴቶችም ወንዶችም የሚደፈሩበትና ከዘረኞች ጥቃት የሚያወጣቸዉ ድርጂት አለመገኘቱ በጣም አሰቃአሊ እና አሳዛኝ እንደሆነ፤ ማንኛዉም ሰዉ ቢመቸዉና የእድገት ሁኔታ ቢከሰት በአገሩ መኖርን እንደሚመርጥ፤ ዛሬ በዓለም ላይ የምናያቸዉ አህጉራት በሞላ የተሞሉት በ አዉሮፓ የነበረዉን ስቃይና ችግር ሸሽተዉ በተባረሩ መድራሻ ባጡ ሰዎች መሆኑን ማስታወስና ማጤን እንደሚገባ ተገልጽዋል። በተጨመሪም በ ድርሮዋ ዬጎዝላቭያ፤ ሩዋንዳና በ ኮንጎ የተከሰትዉ እንዳገና መከሰት እንደሌለባትና በአገራችን ኢትዮጵያ በአሁኑ ወቅት የተንሰራፋዉ የዘር ፖለቲካና ያስከተለዉ ዘረኝነትና ጥላቻ አስጊ እንዳሆነ ተገልጽዋል።

በአጠቃላዩ እእነዚህ ነጥቦች በሞላ በጽሁፍ እና በዲስኩር ብቻ ሳይሆን ፊት ለፊት በሚገኙት ስፔሻል ራፖርተርስ ጋራም ለመወያየት ተችሏል። በጄኔቫም ከተማ ዋና ቢሮዉ የሚገኘዉም ዬ.ኤን.ኤች.ሲ.አር ቢሮ ቀጠሮ ይዞ በመሄድ ከአዉሮፓ፤ ከአፍሪካእና መካከላኛዉ ምስራቅ ዴስኮች ጋራ ለመገናኘት ተችሏል። ይሄም

በመሆኑ በ ኖርዌና በ ሊብያ ያለዉን በወገኖቻችን ላይ የሚደርሰዉን በደልና የሰባዓዊ መብት ረገጣ በተማለከተ ዘገባዎችን ለማቅረብ ተችሏል።


UN ACTION AGAINST SEXUAL VIOLENCE IN CONF
THERE CAN BE
NO SECURITY
WITHOUT
WOMEN'S
SECURITY
www.stoprapenow.org



